# የገቢ ዕቃዎች የትራንዚት

# ትራንስፖርት ሥርዓት መመሪያ

**317/2013**

የካቲት 2005
አዲስ አበባ

# የገቢ ዕቃዎች የትራንዚት ትራንስፖርት ሥርዓት መመሪያ

## መግቢያ

ኢትዮጵያ ለባለፉት ዘጠኝ ዓመታት እያስመዘገበች ባለዉ ፈጣን ዕድገት ሳቢያ በተፈጠረው የኢኮኖሚ መነቃቃት ወደ አገር ውስጥ የምታስገባቸውም ሆነ የምትልካቸው ዕቃዎች መጠን ከጊዜ ወደ ጊዜ እያደገ ነው፡፡ ይኸም ዕድገት በአጭር ጊዜ ውስጥ በእጥፍ እንደሚያድግ ይገመታል፡፡ በአንፃሩ ዕቃን ከወደብ የማንሳት አቅማችን በዚያው መጠን ባለማደጉ እና ከአስመጪው ጀምሮ በሂደቱ ተዋናይ በሆኑ አካላት ላይ ከሚታዩ ድክመቶችና ችግሮች፣ የማጓጓዝ ሥርዓቱ ፈጣን ካለመሆኑ የተነሳ፣በአገር ዉስጥ በቂ የማከማቻ መጋዘን ባለመኖሩ የገቢ ንግድ ዕቃዎቻችን ለከፍተኛ የመጋዘን ኪራይ እና ከቆይታ ብዛት ለብልሽት ከመጋለጣቸዉም በላይ ለወደብ መጨናነቅ፣ዕቃዎች በተገቢ ጊዜ አገር ዉስጥ ገብተው ለተገልጋዩ አለመድረስ ከዚህም ጋር ተያይዞ ለሚፈጠር የዕቃዎች እጥረት የዋጋ ዉድነት፣ፋብሪካ ምርቶች መቋረጥ፣የግንባታዎች መዘግየት እንዲሁም ለልዩ ልዩ አላስፈላጊ ወጪዎችና መሠል ጉዳቶች እንዲከሰቱ ምክንያት በመሆን ላይ ነው፡፡ ከዚህም ባለፈ ዕቃዎች ወደብ ላይ ከ6 ወር በላይ በመቆየታቸው በወደብ ተወርሰው በጨረታ የመሸጥ ሁኔታ የሚደጋገም ክስተት የነበረ መሆኑ የሚታወስ ነው፡፡

ስለሆነም እነዚህን ችግሮች እና ማነቆዎች ለመፍታት ተገቢ የሆነ ስትራቴጂ በማዘጋጀት ለተግባራዊነቱ መጣር ግድ ከማለቱም በላይ የአገራችን የገቢ ዕቃዎች በወደብ ላይ ለረጅም ጊዜ የማይከማቹበትን አሰራር በመዘርጋት ከገቢ ዕቃዎች ጋር ተያይዘዉ የሚከሰቱ ችግሮችን በዘላቂነት መፍታት አስፈላጊ ነዉ፡፡

የአገራችንን የገቢ ዕቃዎች ንግድ ልማት ለመደገፍ መከናወን ካለባቸው ቁልፍ ተግባራት ውስጥ አንዱ የትራንዚት ወጪና ጊዜን ለመቀነስ የሚያስችል የትራንዚት ሥርዓት እና የገቢ ዕቃዎችን ወደ አገር ዉስጥ በአጭር ጊዜ ለማጓጓዝ የሚያስችል የአሰራር ሥርዓት መመሪያ አዘጋጅቶ ተግባራዊ ማድረግ ነው፡፡ ከዚህ አኳያ የአገሪቱ የገቢ ንግድ በተፈላጊ ደረጃ ኢኮኖሚያዊ አዋጭነቱ የተረጋገጠ፣ ደህንነቱ የተጠበቀ እና ቀልጣፋ የወደብና የትራንዚት አገልግሎት እንዲያገኝ የሚያስችል እንዲሁም የገቢ ዕቃዎች

ክምችት እንዳይኖር የሚያደርግ የአሠራር  መመሪያ ሥራ ላይ እንዲውል በማድረግ የገቢ ንግዳችንን ኢኮኖሚያዊ አዋጭነት ያለዉ ማድረግ የግድ ይላል፡፡

በዚህ መሠረት የገቢ ዕቃዎች ትራንዚትን ሂደት ለመከታተል የሚያስችል አሠራር የሚመራበትን ስታንዳርድ እና አሠራር ሥርዓት ተግባራዊ ለማድረግ እና የሚመለከታቸው አካላት እስካሁን ተግባራዊ እያደረጉ የቆዩት ተግባርና ኃላፊነት እንደተጠበቀ ሆኖ የገቢ ዕቃዎች ከወደብ በአፋጣኝ የማንሳት ዓላማ ለማሳከት ይቻል ዘንድ  የሚጠበቅባቸውን ሃላፊነቶችና ግዴታዎች ለመወሰን ይህ መመሪያ ወጥቶ ሥራ ላይ እንዲውል ተወስኗል፡፡ ይህ መመሪያ በማሪታይም ዘርፍ አስተዳደር አዋጅ ቁ.549/1999 አንቀጽ 6 ሥር በተደነገገው መሠረት በወደብና በትራንዚት ኮሪደር በሚካሄደው የአገሪቱ የወጪ እና የገቢ ንግድ እንቅስቃሴ በተለይም የአገሪቷን የገቢ ዕቃዎች እንቅስቃሴ ኢኮኖሚያዊነት፣ቀልጣፋነት ለማረጋገጥ እና ለመቆጣጠር እንዲሁም የትራንዚት አገልግሎት ሥርዓት እንዲሳለጥ የገቢ ዕቃዎች ወደብ ላይ እንዳይከማቹ በሚቻልበት አግባብ የሚመለከታቸው አካላት ተቀናጅተው እንዲሠሩ የመከታተል፣ የመቆጣጠርና የመምራት ኃላፊነት በተጣለበት የማሪታይም ጉዳይ ባለስልጣን አስፈጻሚነት ነው፡፡

በዚህ መሠረት የገቢ ዕቃዎች የትራንዚት ሥርዓት መመሪያ እና የአሰራር ስታንዳርድ ተግባራዊ ለማድረግ እና የሚመለከታቸው አካላት የገቢ ንግድ ልማት መስኩ የታለመለትን ዓላማ ያሳካ ዘንድ የሚጠበቅባቸውን ሃላፊነቶችና ግዴታዎች ለመወሰን በማሪታይም ዘርፍ አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 549/1999 አንቀጽ 18 (ለ) ለሚኒስቴሩ በተሰጠው ስልጣን መሠረት ይህ መመሪያ ወጥቷል።

## ክፍል አንድ - ጠቅላላ ድንጋጌዎች

### 1. አጭር ርዕስ

ይህ መመሪያ ‹‹የገቢ ዕቃዎች የትራንዚት ትራንስፖርት ሥርዓት መመሪያ›› ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

### 2. የቃላት ትርጓሜ

የቃሉ አገባብ የተለየ ትርጓሜ የሚያሠጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ መመሪያ ውስጥ፦

2.1. **ገቢ ጭነት** ማለት በኮንቴይነርና ከኮንቴይነር ውጪ ከተለያዩ ሀገሮች ወደ ሀገር ውስጥ የሚገቡ ዕቃዎች ማለት ነው፤

2.2. **የባንክ ፈቃድ** ማለት ማንኛውም አስመጪ ዕቃዎችን ከውጭ ሀገር በመግዛት ወደ ሀገር ውስጥ ለማስገባት ከባንኮች የውጭ ምንዛሬ ፈቃድ እና ሌሎችንም ድጋፍ የሚያገኝበት ስርዓት ነው፡፡

2.3. **የእፎይታ ጊዜ** ማለት በባህር ወደብ ዕቃዎች ያለ መጋዘን ኪራይ እንዲቆዩ ለአስመጪዎች በባለ ወደብ ሀገራት በኩል የተፈቀደ ጊዜ ነው፡፡

2.4. **የዕቃ አስተላላፊነት ውክልና** ማለት በአገር ውስጥ ወይም በዓለም አቀፍ ደረጃ ዕቃ ተቀባይን ወይም ዕቃ ላኪን በመወከል የጉምሩክ ሥነ-ሥርዓት፤ የወደብ ሥነ-ሥርዓት እና ሌሎች ሥነ-ሥርዓቶችን አስፈጽሞ የገቢ ወይም የወጪ ዕቃዎች በወደብ እንዲገቡ ወይም እንዲወጡ ማድረግ ሲሆን ዕቃን የማጓጓዝንና የማስረከብን ሥራ ይጨምራል፤

2.5. **ዕቃ አስተላላፊ** ማለት በዕቃ አስተላላፊነት እና የመርከብ ውክልና ሥራ ፈቃድ በሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁ.37/1990 መሠረት የዕቃ አስተላላፊነት ለመሥራት የንግድ ፈቃድ የተሰጠው ሰው ነው፤

2.6. **የመርከብ ውክልና** ማለት የመርከብ ባለንብረትን፤ ተከራይን፤ ወይም አከናዋኝ በመወከል፤ መርከቡ የሚያጓጉዘውን ዕቃ ወይም መንገደኛ ማግኘትንና መመዝገብን፤ በባህር ወደብ ላይ እና በአገር ውስጥ ለመርከቦች አገልግሎት መስጠትን፤እንዲሁም መሰል ተግባራት ማከናወንን ይጨምራል፡፡

2.7. **የመርከብ ወኪል** ማለት በዕቃ አስተላላፊነት እና የመርከብ ውክልና ሥራ ፈቃድ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁ.37/1990 መሠረት በመርከብ ውክልና ለመሥራት የንግድ ፈቃድ የተሰጠው ሰው ነው፤

2.8. **የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት** ማለት በገቢ ዕቃዎች የትራንዚት ትራንስፖርት ስርዓት መመሪያ በተወሰነው እና ሚኒስቴሩ ወደፊት በሚያወጣው መመሪያ በሚወሰነው መሰረት በዕቃ አስተላላፊነት ፣ በመርከብ ውክልና ፣ እንዲሁም በሌሎች ዘርፉ የተመለከቱ የንግድ ሥራዎች ላይ ለመሰማራት የሚያበቃ የሙያ ብቃት ያላቸው ሠራተኞች ፣ የቢሮ አደረጃጀት መሟላቱን፣ የካፒታል አቅም መኖሩን እና የአሠራር ሥርዓት መኖሩን ለማረጋገጥ በማሪታይም ጉዳይ ባለስልጣን የሚሰጥ ማስረጃ ነው፤

2.9. **ድርጅት** ማለት የኢትዮጵያ የባሕር ትራንስፖርትና ሎጂስቲክስ አገልግሎት ድርጅት ሲሆን በሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 255/2004 የተቋቋመው የመንግሥት የልማት ድርጅት ነው፤

2.10. **አዋጅ** ማለት የማሪታይም ዘርፍ አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 549/1999 ነው፤

2.11. **ሚኒስቴር ወይም ሚኒስትር** ማለት የትራንስፖርት ሚኒስቴር ወይም ሚኒስትር ነው፤

2.12. **ባለሥልጣን** ማለት በማሪታይም ዘርፍ አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 549/1999 መሠረት የተቋቋመው የማሪታይም ጉዳይ ባለሥልጣን ነው፤

2.13. **ታሪፍ** ማለት የገቢ ዕቃዎች ትራንዚት ስርዓትን ለመፈጸም የዕቃ አስተላላፊው ወይንም የመርከብ ወኪሉ ከዕቃ አስመጪው ጋር በሚያደርገው ውል መሰረት የሚጠቀምበት የውል ሁኔታ ሆኖ በተለይም ለአገልግሎት ክፍያ የሚጠየቅ ነው፡፡

2.14. **ሰው** ማለት የተፈጥሮ ሰው ወይም በሕግ የሰውነት መብት የተሰጠው ሰው ነው፡፡

## 3. የመመሪያው ዓላማ

የገቢ ዕቃዎች ትራንዚትና ትራንስፖርት ሥርዓት መመሪያ ዋና ዓላማ የሀገሪቱ የገቢ ዕቃዎች የትራንዚት ትራንስፖርት አገልግሎት የትራንዚት ጊዜና ወጪ ለመቀነስ የሚያስችል እና ኢኮኖሚያዊነትና ቀልጣፋነትን ለማረጋገጥ፣ በዕቃዎች የወደብ ላይ ቆይታ ምክንያት የሚደረግ የመጋዘን ወጪን ለመቀነስ፣ ዕቃዎች በወቅቱ ተጓጉዘው ለተፈለገው ዓላማ እንዲደርሱ ለማድረግና  እንዲሁም የወደብ መጨናነቅ እንዳይፈጠር ለማድረግ  ነው፡፡

## 4. አስፈጻሚ አካል

በአዋጁ አንቀጽ 6 ንዑስ አንቀጽ 1፣ 2፣ 8፣ 19 ሥር በተደነገገው መሠረት የማሪታይም ጉዳይ ባለስልጣን የገቢ ዕቃዎች የትራንዚት ሥርዓት የሚመራበትን አሠራር ለመወሰን የወጣውን ይህን መመሪያ የማስፈጸም ስልጣን እና ኃላፊነት ተሰጥቶታል፡፡

## 5. የተፈጻሚነት ወሰን

ይህ መመሪያ ተፈጻሚነት የሚኖረው በባህር ትራንስፖርት ተጓጉዘው  ወደ ኢትዮጵያ በሚገቡ  ዕቃዎች ላይ ነው፡፡

# ክፍል ሁለት

## መመሪያው የሚመለከታቸው አካላት ኃላፊነትና ተግባር

### 6. የሚኒስቴሩ ተግባርና ኃላፊነት

ሚኒስቴሩ የሎጅስቲክስ እና የትራንዚት ትራንስፖርት ወጪና ጊዜን ከመቀነስ አንፃር ከፍተኛ ሚና ያለውን የሀገር ውስጥ መጋዘን አስተዳደር ሥርዓት ይዘረጋል፡፡

### 7. የማሪታይም ጉዳይ ባለስልጣን ተግባር እና ኃላፊነት

ይህንን መመሪያ በተመለከተ ባለስልጣኑ የሚከተለው ኃላፊነት ይኖረዋል፡፡

7.1. የገቢ ዕቃዎች የትራንዚት ትራንስፖርት አገልግሎት አሰጣጥ ስታንዳርድ በማዘጋጀት ሥራ ላይ እንዲውል ያደርጋል አፈጻጸሙን ይከታተላል ፤ ይቆጣጠራል ፤እንዲሁም ስታንዳርዱን ያሻሽላል፡፡

7.2. የገቢ ዕቃዎች የትራንዚት ትራንስፖርት አገልግሎት ስርዓት በሚመለከት፤ የትራንዚት ወጪ ስታንዳርድ ያዘጋጃል፣ አፈጻጸሙን ይከታተላል፣ ይቆጣጠራል፡፡

7.3. በሀገር ውስጥ በዕቃ አስተላላፊነት ውክልና እና በመርከብ ውክልና የአገልግሎት መስክ የተሰማሩትን እና ወደፊት ወደ መስኩ ለመግባት ማመልከቻ የሚያቀረቡትን በመገምገም ብቁ የሆኑትን በመለየት የብቃት ማረጋገጫ ማስረጃ የተሰጣቸውን አከናዋኞች የተመለከተ ወቅታዊ መረጃ እያደራጀ ለላኪዎች፣ ለኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን፣ ለንግድ ሚኒስቴር፣ ለወደብ ባለስልጣናት እና ለሌሎች ለሚመለከታቸው አካላት ይሰጣል፡፡

7.4. በተራ ቁጥር 7.3. ተለይተው በአገልግሎት ዘርፍ ፈቃድ ያገኙና ያደሱ የዕቃ አስተላላፊ አካላት ወደቡ ከሚገኝበት ሀገር የዕቃ አስተላላፊዎች ጋር ተቀናጅተው ለመስራት ውል የገቡበትን እና የኩባንያዎችን ዝርዝር መረጃ ማስመዘገባቸውንና በየጊዜው ወቅታዊ መሆኑን ይቆጣጠራል፡፡

7.5. የዕቃ አስታላላፊና የመርከብ ወኪሎችን የአገልግሎት አሰጣጥ የብቃት ስታንዳርድ በማዘጋጀት ሥራ ላይ ያውላል፡፡

7.6. በተራ ቁጥር 7.5 በተዘጋጀው የአገልግሎት አሰጣጥ ስታንዳርድ መሠረት የዕቃ አስታላላፊነትና የመርከብ ወኪሎች ኩባንያዎች አሠራር ከሚመለከታቸው ጋር በጋራ በመሆን ግምገማ በማድረግ ማበረታቻና ዕውቅና የሚሰጥበት ሥርዓት ይዘረጋል፡፡ በተቀመጠው የአገልግሎት አሰጣጥ ብቃት ስታንዳርድ መሠረት ብቁ ሆኖው ያልተገኙ እና በመስኩ እንዳይሰማሩ የሥራ ፍቃድ የታገደባቸውን/ የተሰረዘባቸውን/ አገልግሎት ሰጪዎች ዝርዝር ለሚመለከታቸው ተጠቃሚዎችና ተቆጣጣሪ መ/ቤቶች በወቅቱ ይፋ ያደርጋል፡፡

7.7. ሀገራዊ የማሪታይም ሎጅስቲክስ መረጃ ሥርዓት በመዘርጋትና በዘመናዊ ቴክኖሎጂ በመደገፍ በየዕለቱ ከኢትዮጵያ የባህር ትራንስፖርትና ሎጅስቲክስ አገልግሎት ድርጅት፣ ከኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን፣ ከዕቃ አስተላላፊዎች እና ከመርከብ ወኪሎች የገቢ ዕቃዎችን መጠን በዕቃ ዓይነት በመለየት፣ በኦፕሬሽን ላይ ያጋጠሙ ችግሮችን፣ እንዲሁም በባህር ወደብ ላይ ስለተከማቹ ገቢ ዕቃዎች ከተለያዩ አካላት የሚላከውን መረጃ በወቅቱ መላኩን ይከታተላል ያጠናቅራል

7.8. ለ45 ቀናት እና ከዚያ በላይ የቆዩ ዕቃዎችን በመለየት አስመጪዎቹ ዕቃዎቻቸውን በተለያየ ደረጃ እና መንገድ ጭነቱን ከባህር ወደብ እንዲያነሱ ክትትል ያደርጋል፤ የአሰራር ሥርዓት ይዘረጋል

7.9. ዕቃዎቻቸውን በወቅቱ ከባህር ወደብ ያላነሱ አስመጪዎችን የችግሮች ምንጭ በመለየት መፍትሄ ይሰጣል ከአቅም በላይ የሆኑትን ለበላይ አካል ያሳውቃል፤

7.10. በየወሩ አስመጪዎች ዕቃዎቻቸውን እንዲያነሱ በተደረገው ጥረት ውስጥ ምን ያህል መጠን ዕቃ ከወደብ እንደተነሳ ፣ የተገኙ ውጤቶች እና ያጋጠሙ ችግሮችን በግልጽ በመለየት (የአፈጻጸም ሪፖርት) ለትራንስፖርት ሚንስቴር እና ለሚመለከታቸው አካሎች ያቀርባል፤

7.11. በሂደቱ ውስጥ ያጋጠሙ ችግሮችን እንዲሁም ከችግሮቹ በመነሳት የፖሊሲ ወይም የአሠራር ለውጥ የሚያስፈልጋቸውን ቁልፍ ጉዳዮች በመለየት ችግሩን በማጥናት የመፍትሄ ሃሳብ በማካተት ለሚ/ር መ/ቤቱ በማቅረብ እና በጥናት ውጤቱ በመመስረት እንዲፈጸም ያደርጋል፤

7.12. ተደጋጋሚ ድጋፍ ተደርጎላቸው በባህር ወደብ ላይ ዕቃቸውን በ60 ቀናት ውስጥ ያለበቂ ምክንያት የማያነሱ አስመጪዎችን መረጃ በማጠናቀር እርምጃ እንዲወሰድባቸው ለብሔራዊ ባንክ ያሳውቃል፡፡

7.13. የገቢ ዕቃዎች የትራንዚት ትራንስፖርት በተመለከተ በባህር ወደብ የሚያጋጥሙ ማነቆዎችን መለየት፣ እንዲሁም የወደብና የትራንዚት አገልግሎት በሚሻሻልበት ዙሪያ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር ድርድርና ምክክር በማድረግ የሚያጋጥሙ ችግሮችን ይፈታል፤ የባህር ወደብ አጠቃቀም ስምምነት ያደርጋል ፤ ይከታተላል ፤ ያሻሽላል።

7.14. ይህ መመሪያ በአግባቡ ሥራ ላይ መዋሉን እየተከታተለ ለትራንስፖርት ሚኒስቴርና ለሚመለከታቸው አካላት ይልካል፡፡

# 8. <u>የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን ተግባር እና ኃላፊነት</u>

ይህንን መመሪያ በተመለከተ የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን የሚከተለው ኃላፊነት ይኖረዋል።

8.1. ዕቃ ከመድረሱ በፊት በሚያገኘው የመርከብ ጭነት መረጃ /Cargo Manfest/ መሰረት ትራንዚት በአግባቡ ያጠናቀቁና ያላጠናቀቁ የመከታተል እንዲሁም በየዕለቱ በወደብ የተራገፈው ገቢ ዕቃ ከተራገፈው ውስጥ የተነሳውን እና ያልተነሳውን የጭነት መረጃ የመያዝ ይህንኑ የወደብ መረጃ (Port Position) ለማሪታይም ጉዳይ ባለስልጣን እና ለሚመለከተው አካል ያሳውቃል፡፡

8.2. የገቢ ንግድን በተመለከተ ከማሪታይም ጉዳይ ባለስልጣን ከሚላክለት የዕቃ አስተላላፊዎች ዝርዝር ውጪ ሌሎች በዚህ አገልግሎት እንዳይሰማሩ ያደርጋል፡፡

8.3. የገቢ ዕቃዎች ትራንዚት ትራንስፖርትን በተመለከተ ከጉምሩክ አሰራር ጋር የተያያዙ ማነቆዎችን ይፈታል።

## 9. የትራንስፖርት ባለስልጣን ሃላፊነትና ተግባር

የትራንስፖርት ባለስልጣን ይህን መመሪያ በተመለከተ የሚከተለው ሃላፊነትና ተግባር ይኖረዋል፡፡

9.1. በደረቅና ፈሳሽ ጭነት ማጓጓዝ የተሰማሩ አገልግሎት ሰጪ የተሽከርካሪ ባለንብረት ተቋማት ስታንዳርድ ያዘጋጃል ፤ ይከታተላል ፤ ይቆጣጠራል፡፡

9.2. ሀገራዊ የፖሊሲ አቅጣጫን ተከትሎ ወቅታዊ ምላሽ ለመስጠት የሚያስችል የጭነት ተሽከርካሪ ሀብትን የማንቀሳቀስ /Resource Mobilization/ አሰራር ስርዓት ይዘረጋል ፤ ይከታተላል ፤ ይቆጣጠራል፡፡

## 10.የኢትዮጵያ የባህር ትራንስፖርትና ሎጅስቲክስ አገልግሎት ድርጅት ተግባር እና ኃላፊነት

ድርጅቱ በዕቃ አስተላላፊነት እና በመርከብ ውክልና አገልግሎት ሰጪነቱ የሚጠበቅበት ግዴታና ሃላፊነት እንደተጠበቀ ሆኖ ይህንን መመሪያ በተመለከተ የሚከተለው ኃላፊነት ይኖረዋል፡፡

10.1. የድርጅቱ ንብረት በሆኑ መርከቦችና፣ በድርጅቱ ኃላፊነት በሌሎች የመርከብ ኩባንያዎች/ድርጅቶች/ የሚጓጓዝ የገቢ ዕቃዎች መረጃ በተሟላ መልኩ በማጠናቀር በየዕለቱ ለማታይም ጉዳይ ባለስልጣንና ለገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን ይልካል፡፡

10.2. የገቢ ዕቃ ጭነቶች ባህር ወደብ ከመድረሳቸው በፊት ግምታዊ የዕቃ መድረሻ ጊዜ (Expexted time arrival) ለአስመጪዎች ያሳውቃል፡፡

10.3. በድርጅቱና በእሱ ኃላፊነት የተጓዙ ከወደብ ሳይነሳ 30 ቀናትና ከዚያ በላይ የቆዩ ዕቃዎችን በመለየት እና ዝርዝር የአስመጪዎች አድራሻ መረጃ በማካተት ለባለስልጣኑ በየዕለቱ ይሰጣል፡፡

10.4. ስድስት ወራት እና ከዚያ በላይ በባህር ወደብ የተከማቹ ገቢ ዕቃዎችን በተመለከተ በገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር መመሪያ መሰረት ተፈፃሚ ያደርጋል፡፡

## 11. የዕቃ አስተላላፊ ተግባር እና ኃላፊነት

በሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁ.37/1990 የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ ይህንን መመሪያ በተመለከተ ማናቸውም የዕቃ አስተላላፊ የሚከተለው ኃላፊነት ይኖረዋል፡፡

11.1. አግባብ ባላቸው ሕጎች፣ ደንቦችና በዚህ የገቢ እቃዎች የትራንዚት ትራንስፖርት ሥርዓት መመሪያና ስታንዳርድ መሠረት ይሰራል፡፡

11.2. አስመጪውን በመወከል የወደብ ታሪፍና በትራንዚት ሂደቱ ውስጥ የሚኖሩ የሶስተኛ ወገን ታሪፎችን የመቆጣጠር፣ ተገቢነት የሌለው ወጪ የማስቀረት፣ ዕቃው በመያዣነት በባህር ወደብ እንዳይታገት ያደርጋል፡፡

11.3. ከላይ በተራ ቁ.11.2. በተመለከተው መሠረት ትክክለኛ መረጃ በማቅረብ ማስመዝገብ እና ወቅታዊ መረጃና ለውጥ ለማሪታይም ጉዳይ ባለስልጣን ይሰጣል፡፡

11.4. ከአስመጪው አስፈላጊ ሰነዶችን ከተረከበ በኋላ ተገቢውን የጭነት መረጃዎችን በተሟላ መልኩ መስጠት እና አስመጪው በተሟላ መረጃ ላይ ተመስርቶ የአስመጪነት ሥራውን እንዲሰራ ይደግፋል፡፡

11.5. በየዕለቱ የገቢ ዕቃዎችን መጠን እና ኦፕሬሽን ላይ ያጋጠሙ ችግሮችን በተዘረጋው ሥርዓት መሠረት በወቅቱ ለማሪታይም ጉዳይ ባለሰልጣን መረጃውን ያስተላልፋል፡፡

11.6. ሰነዶች እና ጭነቱን ከባህር ወደብ ለማንሳት የሚያስፈልጉ መረጃዎች ከአስመጪው ከተረከበ በኋላ የወደብና የጉምሩክ ፎርማሊቲ በወቅቱ በማጠናቀቅ ዕቃዎቹ ወደ ሀገር ውስጥ በስታንዳርዱ መሰረት እንዲጓጓዙ ያደርጋል፡፡

## 12. የመርከብ ወኪል ተግባር እና ኃላፊነት

በሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁ. 37/1990 የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ ይህንን መመሪያ በተመለከተ ማንኛውም የመርከብ ወኪል የሚከተለው ኃላፊነት ይኖረዋል፡፡

12.1. በሚወክለው የመርከብ ኩባንያ የተጓጓዘ የኢትዮጵያ ጭነት መረጃ በየዕለቱ ለማሪታይም ጉዳይ ባለሰልጣን እና ለደንበኞች ያሳውቃል፡፡

12.2. የመርከብ ወኪሉ በሚወክለው መርከብ የሚጓጓዙ የገቢ ዕቃዎች መረጃ በተሟላ መልኩ በማጠናቀር በየዕለቱ ለማሪታይም ጉዳይ ባለስልጣን ይልካል፡፡

12.3. የመርከብ ወኪሉ በሚወክለው መርከብ የሚጓጓዙ ገቢ ዕቃዎች ወደብ ሊደርስ የተቃረበው ወይም የደረሰ ጭነትን መረጃ በተመለከተ አስመጪዎች እንዲያውቁት ያደርጋል

12.4. የመርከብ ወኪሉ በሚወክለው መርከብ የተጓጓዙ የገቢ ዕቃዎች ከወደብ ሳይነሳ 30 ቀናትና ከዚያ በላይ የቆዩ ዕቃዎችን በመለየት እና ዝርዝር የአስመጪዎች አድራሻ መረጃ በማካተት ለማሪታይም ጉዳይ ባለስልጣን በየዕለቱ ይሰጣል፡፡

## 13. የኢትዮጵያ ብሄራዊ ባንክ ተግባር እና ኃላፊነት

ይህን መመሪያ በተመለከተ የብሄራዊ ባንክ የሚከተለው ኃላፊነት ይኖረዋል፡፡

13.1. ከወደብ ዕቃዎቻቸውን በተደጋጋሚ በወቅቱ የማያነሱ አስመጪዎች ተጠያቂ የሚያደርግ የአሠራር ሥርዓት ይዘረጋል ፡፡

13.2. በየዕለቱ ለገቢ ዕቃዎች የተሰጡ የባንክ ፈቃዶችን በዕቃ ዓይነት በመለየት ሁሉም ባንኮች ለባለስልጣኑ መረጃውን እንዲልኩ ያደርጋል ይቆጣጠራል፡፡

## 14. የባንኮች ተግባር እና ኃላፊነት

ይህን መመሪያ በተመለከተ ባንኮች የሚከተለው ኃላፊነት ይኖረዋል፡፡

14.1. በየዕለቱ ለገቢ ዕቃዎች የተሰጡ የባንክ ፈቃዶችን በዕቃ ዓይነት እና በመጠን በመለየት ለባለስልጣኑ መረጃውን ያስተላልፋል፡፡

14.2.የአስመጪዎችን አስፈላጊ ሰነዶች (Bill of Loading) በወቅቱ ሰነዶቹ መድረሳቸውን ያሳውቃሉ፡፡

14.3. የባንክ ፈቃድ በሚሰጥበት ወቅት የአስመጪዎችን የተሟላ አድራሻ ይመዘግባል፡፡

## 15. የማስፈጸሚያ ስልቶች

ከዚህ መመሪያ ጋር በክፍል ሶስት አባሪ ሆነው የተያያዙት የገቢ ዕቃዎች ትራንዚትና ትራንስፖርት ሂደት ለመከታተል የሚያስችሉ የአሰራር ስታንዳርዶች፣ የዚህ መመሪያ አካል ሆነው ይፈጸማሉ፡፡

15.1. በባህር ወደብ ላይ ከሰላሳ ቀናት በታች ለቆዩ ገቢ ዕቃዎች በተመለከተ ተፈጻሚ የሚሆን

15.2. በባህር ወደብ ላይ ከሰላሳ ቀናት በላይ ለቆዩ ገቢ ጭነቶች በተመለከተ ተፈጻሚ የሚሆን

15.3. ባህር ወደብ ላይ ከስድስት ወራት በላይ ለቆዩ ገቢ ጭነቶች በተመለከተ ተፈጻሚ የሚሆን

## 16. መመሪያው የሚጸናበት ጊዜ

ይህ መመሪያ ከዛሬ ቀን 2005 ዓ.ም. ጀምሮ የጸና ይሆናል፡፡

አዲስ አበባ--------ቀን 2005 ዓ.ም

ድሪባ ኩማ

የትራንስፖርት ሚኒስትር

# ክፍል ሶስት

## የገቢ ዕቃዎች ትራንዚት አገልግሎት ሥርዓት አፈጻጸም ስታንዳርድ

### መግለጫ

የገቢ ጭነት ትራንዚት ትራንስፖርት ሥርዓት መመሪያን ለማስፈጸም እና በመመሪያው ውስጥ ሃላፊነትና ተግባር የተሰጣቸው አካላት ኃላፊነቶቻቸውን በአግባቡ ማከናወናቸዉን ለመከታተልና አፈጻጸማቸውን ለመለካት እንዲያስችል ይህ ወጥ የሆነ የገቢ ዕቃዎች የትራንዚት ትራንስፖርት ሥርዓት ስታንዳርድ ተዘጋጅቷል፡፡

ስታንዳርዱ ሲዘጋጅ በዋናነት መሰረት ያደረገዉ በገቢ ዕቃዎች ትራንዚት ትራንስፖርት ጊዜ እና ወጪን ከመቀነስ አንጻር የተደረገ ጥናትን፣ በዚህ ደረጃ በጥናት የተገኘውን አማካይ ውጤት መሰረት በማድረግ ፤ በስታንዳርዱ ላይ የዘርፉን ተዋናይ አካላትን አስተያት በማካተት እና የፈጻሚ አካላትን ስምምነት በመዉሰድ ነዉ፡፡

በመሆኑም ስታንዳርዱ የስራው ሂደት የሚወስደውን ጊዜና ቅድመሁኔታ እንዲሁም የተግባሩን ፈጻሚ አካል በግልጽ በማስቀመጥ እና በዕቃዎች የወደብ ላይ ቆይታ ጊዜ መሠረት በሦስት ደረጃ በመለየት እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡

15.1. በባህር ወደብ ላይ ከሰላሳ ቀናት በታች ለቆዩ ገቢ ዕቃዎች በተመለከተ ተፈጻሚ የሚሆን

| ተ/ ቁ | የትራንዚት ፕሮሲጀር | የጊዜ ስታንዳርድ | የሥራው ባለቤት |
|---|---|---|---|
| 1. | የባንክ ፈቃድ ማግኘት፣ ተዛማጅ ፎርማሊቲዎችን ማጠናቀቅ እና የባንክ ፈቃድ መረጃ ለማሪታይም ጉዳይ ባለስልጣን መላክ | የባንክ ፈቃድ ከተሰጠ በ24 ሰዓት ውስጥ | አስመጪ/ባንክ |
| 2. | ጭነቶቹ ባህር ወደብ ከመድረሳቸው በፊት /Expected Arrival Time/ ለአስመጪው እና ለገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን ማሳወቅ | መርከቡ ባህር ወደብ ከመድረሱ ከ1 ሳምንት በፊት | የባህር አጓጓዥ እና መርከብ ወኪል |
| 3. | ዝርዝር በወደብ የተራገፉ የጭነት መረጃ ለማሪታይም ጉዳይ ባለስልጣን መላክ | በየዕለቱ | የባህር አጓጓዥ እና መርከብ ወኪል |
| 4. | የንግድ ባንኮች Bill if loading በደረሳቸው በአንድ ቀን ውስጥ ለአስመጪዎች ማሳወቅና አስፈላጊ ፎርማሊቲዎችን አጠናቆ ከንግድ ባንኮች የጭነት ሰነድ መውሰድ | 1 ቀን | አስመጪ/ ባንክ |
| 5. | ሰነዶችን አሟልቶ ለዕቃ አስተላላፊ Forwarding Instruction መስጠት | ከባንክ ሰነዱን በወሰደ በ1 ቀን ውስጥ | አስመጪ |
| 6. | የጉምሩክ የትራንዚት ፈቃድ ማጠናቀቅ እና የትራንዚት ፈቃድ በወደቡ ለሚገኝ የማሪታይም ጉዳይ ባለስልጣን ማስተባበሪያ ጽ/ቤት እና ለዕቃ አስተላላፊ መስጠት | Forwarding Instruction በተሰጠ በ3 ቀን ውስጥ | የዕቃ አስተላላፊው እና የኢ.ገ.ጉ.ባ |

| ተ/ቁ | የትራንዚት ፕሮሲጀር | የጊዜ ስታንዳርድ | የሥራው ባለቤት |
|---|---|---|---|
| 7. | የባህር ወደብ ፎርማሊቲ አጠናቆ ለጭነት ዝግጁ ማድረግ | 2 ቀን | የባለወደብ ሀገራት ትራንዚተር/ የዕቃ አስተላላፊው |
| 8. | ተሽከርካሪ ማዘጋጀት እና አስፈላጊ ሰነዶችን አሟልቶ ጭነቱን ተሽከርካሪ ላይ መጫን | የባህር ፎርማሊቲ በተጠናቀቀ በ2 ቀን | የባለወደብ ሀገራት ትራንዚተር/ የዕቃ አስተላላፊው |
| 9. | ጭነቱን ተረክቦ ማጓጓዝ | 2 1/2 ቀን | ትራንስፖርተር |
| 10 | የመንገድ ወረቀት ለፎርዋርደር መስጠትና ፎርዋርደሮች ሰነድ እንዲቀረቡ ፍተሻ ማጠናቀቅ | ሰነድ በቀረበ በ1 ቀን | የዕቃ አስተላላፊው/ የኢ.ገ.ጉ.ባ |
| 11 | አስፈላጊ ፎርማሊቲዎችን አሟልቶ ዕቃውን ከጉምሩክ ክልል ማውጣት | ፍተሻ በተጠናቀቀ በ½ ቀን | የዕቃ አስተላላፊው/ አስመጪ |

## 15.2. በባህር ወደብ ላይ ከሰላሳ ቀናት በላይ ለቆዩ ገቢ ጭነቶች በተመለከተ ተፈጻሚ የሚሆን

| ተ/ቁ | የትራንዚት ፕሮሲጀር | የጊዜ ስታንዳርድ | የሥራው ባለቤት |
|---|---|---|---|
| 1. | ጭነቶቹ ባህር ወደብ መድረሳቸውን ለአስመጪው ማሳወቅ | መርከቡ ባህር ወደብ ከደረሰ በ24 ሰዓት ውስጥ | የባህር አጓጓዥ እና መርከብ ወኪል |
| 2. | ጭነቶቻቸውን ያላነሱ አስመጪዎች እንዲያነሱ ማሳሰብ | 8-30 ቀናት | የባህር አጓጓዥ እና መርከብ ወኪል |
| 3. | ጭነቶችን በወደብ ላይ ለሰላሳ ቀናት ያላነሱ አስመጪዎች ዝርዝር መረጃ ለማ.ጉ.ባ ለእርምጃ አወሳሰድ በሚመች መልኩ አጠናቅሮ መላክ | በየዕለቱ | ኢ.ባ.ት.ሎ.አ.ድ/ የመርከብ ወኪል |
| 4. | በሚገኘው መረጃ መሠረት አስመጪዎችን ጭነቶችን እንዲያነሱ ግፊት ማድረግ | በየዕለቱ | ማ.ጉ.ባ |
| 3. | ከሁለት ወር በላይ በባህር ወደብ ላይ ዕቃቸውን ያላነሱ አስመጪዎች ዝርዝር በመለየት ለብሔራዊ ባንክ፣ ለትራንፖርት ሚንስቴርና ለሚመለከታቸው አካላት ሪፖርት ማድረግ | በየ15 ቀን | ማ.ጉ.ባ |

15.3. ባህር ወደብ ላይ ከስድስት ወራት በላይ ለቆዩ ገቢ ጭነቶች በተመለከተ ተፈጻሚ የሚሆን

| ተ/ቁ | የትራንዚት ፕሮሲጀር | የጊዜ ስታንዳርድ | የሥራው ባለቤት |
|---|---|---|---|
| 1. | በባህር ወደብ ላይ ከተራገፉ 30 ቀናት (ለperishable goods) እና 180 ቀናት የሞላቸው ጭነቶችን ዝርዝር (List) ከወደብ ባለሰልጣን ማሰባሰብ | በየዕለቱ | ኢ.ባ.ት.ሎ.አ.ድ |
| 2. | በዝርዝሩ መሠረት የገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን ዴክለራሲዮን መሙላትና የትራንዚት ፈቃድ መጠየቅ | በየዕለቱ | ኢ.ባ.ት.ሎ.አ.ድ |
| 3. | የትራንዚት ፈቃድ መስጠት | 2 ቀን | ኢ.ገ.ጉ.ባ |
| 4. | የትራንዚት ፈቃድ ወደ ጅቡቲ ወደብ መላክ | 1 ቀን | ኢ.ባ.ት.ሎ.አ.ድ |
| 5. | የኮንቴይነር ጭነቶችን ከኮንቴይነር የማውጣት (unstuffing) እና አጠቃላይ የዕቃዎቹ ሁኔታ በመመዝገብ ከወደቡ የዕቃ ርክክብ ሥራ ማከናወን | ከ1-7 ቀን | ኢ.ባ.ት.ሎ.አ.ድ<br>ኢ.ገ.ጉ.ባ |
| 6. | በባህር ወደብ የወደብ ክሊራንስ እና ሌሎች ፎርማሊቲዎችን ማጠናቀቅ | 1 ቀን | ኢ.ባ.ት.ሎ.አ.ድ |
| 7. | ዕቃዎችን ከባህር ወደብ ሲነሱ መረጃዎች በቅድሚያ ለሚራገፍበት ደረቅ ወደብ እና ለማ.ጉ.ባ መረጃ መላክ | በየዕለቱ | ኢ.ባ.ት.ሎ.አ.ድ |

| ተ/ቁ | የትራንዚት ፕሮሲጀር | የጊዜ ስታንዳርድ | የሥራው ባለቤት |
| --- | --- | --- | --- |
| 8. | ጭነቱን ወደ ሀገር ውስጥ ማጓጓዝ | 2 ቀን | ኢ.ባ.ት.ሎ.አ.ድ/ ትራንስፖርተር |
| 9. | የዕቃዎች የርክክብ ሥራ በደረቅ ወደብ ውስጥ ማከናወን | ጭነቱ ከደረሰ ከ 1-2 ቀን | ኢ.ባ.ት.ሎ.አ.ድ እና የኢ.ት.ገ.ጉ.ባ |
| 10. | ዕቃዎቹን ጥቅም ላይ እንዲውሉ ማድረግ | 1-30 ቀናት | ኢ.ባ.ት.ሎ.አ.ድ<br>ኢ.ባ.ት.ሎ.አ.ድ |